የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን በግንቦት ወር አራት፤መደበኛ ጉባኤዎችን ካሂዷል፡፡ በተካሂዱ መደበኛ ጉባኤዎች የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችንና የብድር ስምምነቶችን አጽድቋል፡፡

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ዶ/ር መቅደስ ዳባ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) የ2018 በጀት አመት የ9 ወራት እቅድ አፈጻፀም ሪፖርት ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡

የግንቦት ወር ዜና መጽሔታችን እነዚህንና ሌሎች ምክር ቤታዊ ክንዋኔዎችን የምታስነብብ ይሆናል፡፡

## ዓበይት ርዕሶች

- ሕግ አወጣጥ
- ክትትል ቁጥጥር

መልካም ንባብ!
ግንቦት፤ 2018 ዓ.ም

## ሕግ አወጣጥ

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ግንቦት 06 ቀን 2018 ዓ.ም 21ኛ መደበኛ ጉባኤውን አካሂዷል፤ በዕለቱም የሕብረት ሥራ ማህበራት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አጽድቋል።





ምክር ቤቱ በውሎው የሕብረት ሥራ ማህበራት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅን ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሠለሞን ላሌ ለምክር ቤቱ በንባብ አቅርበዋል፡፡



የተከበሩ አቶ ሠለሞን ላሌ የውሳኔ ሀሳቡን ሲያቀርቡ

የምክር ቤት አባላት በሕብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ ያለው አካል ከማህበሩ ሲለቅ ለስድስት ወራት እንዲቆይ መደረጉ የግለሰቡን መብት የሚጋፋ መሆኑን፣ ኢንቨስተሮች በሕብረት ሥራ ማህበራት ያላቸው ድርሻ አርባ በመቶ መሆኑ የካፒታል አቅርቦትን የሚገድብ መሆኑ፣ በማህበራት ውስጥ ድርሻ ያላቸውን ሴቶች በአመራርነት ቦታ ላይ ያላቸውን ቁጥር እንዲሁም የሕብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ክልልን አስመልክቶ ጥያቄዎች አንስተዋል፡፡

የተከበሩ አቶ ሰለሞን ላሌ በበኩላቸው፣ ከምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ማብራሪያ የማህበራትን የሥራ ክልል አስመልክቶ የቀድሞው አዋጅ ማህበራት እንደ የክልሉ ነባራዊ ሁኔታ እንዲደራጁ የሚፈቅድና በየትኛውም ክልል ተንቀሳቅሶ የመሥራት መብትን የሚገድብ በመሆኑ በዚህ አዋጅ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ቅርንጫፎችን ከፍተው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በማሰብ የተቀመጠ ድንጋጌ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ሌላው በተበታተነ ሁኔታ ተደራጅተው የሚገኙ ማህበራት ስብሰብ ብለው እንዲደራጁና ውጤታማና ትርፋማ እንዲሆኑ ለማስቻል እና ጠንካራ የውስጥ አመራርና የአስተዳደር ሥርዓትን ለመዘርጋት እንዲሁም በሕብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ ያለው አካል

ከማህበሩ ለመውጣት ለግለሰቡ ተመላሽ የሚሆን ገንዘብ እስኪገኝ፣ የማህበሩ ገቢና ወጪ ኦዲት ተደርጎ የካፒታል መጠኑ እስኪታወቅ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ለስድስት ወራት እንዲቆይ የተቀመጠበት አግባብ መሆኑን ገልፀዋል።

አክለውም በማህበራት ውስጥ የሴቶችን የአመራርነት ተሳትፎ በተመለከተ ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል ሴቶች በሚገኙባቸው ማህበራት ላይ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን አንስተዋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው በረቂቅ አዋጁ ላይ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጁን ለማዳበር የሚያግዙ አስተያየቶችን ሲሰበሰብ መቆየቱን የጠቆሙት ሰብሳቢው ማሻሻያ አዋጁ የሕብረት ሥራ ማህበራት ከፋይናንስ ተቋማት ጋር ያላቸውን ትስስር በማጠናከርና የፋይናንስ አቅርቦት ችግራቸውን በመፍታት ተወዳዳሪነታቸውን ከማሳደግ ባሻገር ጠንካራ የኢንስፔክሽን ሥርዓት በመዘርጋት የሕብረት ሥራ ማህበራትን ከብክነትና ምዝበራ በመታደግ ረገድ ሚናው የጎላ መሆኑን አመላክተዋል።

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የሕብረት ሥራ ማህበራት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ረቂቅ አዋጁን፣ አዋጅ ቁጥር 1416/2018 በማደረግ በሙሉ ድምፅ አፅድቋል።



የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

ምክር ቤቱ በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ግንቦት 27 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 23ኛ መደበኛ ጉባኤው የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ አፀደቀ፡፡



የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ፈትሂ ማሕዲ (ዶ/ር) የረቂቅ አዋጆችን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡



ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጆች ላይ ሰፊ ወይይት ካደረገ በኋላ ፡-

•በኢ..ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥትና እና በሴራሊዮን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1417/2018፣ በኢ..ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በአንጎላ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1418 /2018፣ በኢ..ፌ.ዴ.ሪ.

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

መንግሥት እና በባንግላዲሽ ሕዝባዊ ረፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1419/2018፣ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በኢስዋቲን ንጉሠ ነገሥት መንግሥታት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1420/ 2018 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

ምክር ቤቱ በዚሁ ዕለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1421/2018 እንዲሁም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በቬትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል የአገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1422/2018 በማደረግ በሙሉ ድምፅ አፅድቋል።

በተያያዘ ምክር ቤቱ በኢትዮጵያና በአፍርካ ልማት ባንክ መካከል ለአርብቶ አደሩ የምግብና የኑሮ ዘይቤ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅን እና በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ለስድስተኛ ምዕራፍ የልማት ሴፍትኔት ፕሮጀክት የተደረገ የብድር ስምምነት አፅድቋል።

የብድር ስምምነቶቹን በማስመልከት በሕዝበ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር) ባቀረቡት ማብራሪያ ከአፍሪካ ልማት ባንክ ለአርብቶ አደር ምግብና የኑሮ ዘይቤ ማሻሻያ ፕሮጀክት የተገኘው ብድር መንግስት

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የአርብቶ አደሩን የህበረተሰብ ክፍል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመቋቋም የሚያስችሉ የተቀናጁ የልማት ፕሮጀክቶችን የበለጠ እንደሚያግዝ አንስተዋል፡፡



በተያያዘም በኢትዮጵያና በዓለም ዓቀፍ ልማት ማህበር መካከል ስድስተኛውን ምዕራፍ ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት መንግስት በምግብ ዕጥረት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተስብ ክፍሎችን ከዕርዳታ ተጠቃሚነት ወደ ምርታማነት ለማሸጋገር ባለፉት ጊዜያት የልማት ሴፍትኔት ፕሮጀክትን ቀርጾ ተግባራዊ ማድረጉንና ስድስተኛው ምዕራፍ ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት በ12 ክልሎችና በአንድ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ባሉ 494 ወረዳዎች ተግባራዊ እንደሚሆን አመላክተዋል፡፡

በማስከተልም ረቂቅ የብድር ስምምነቶቶቹ ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግረው ዝርዝር ውይይት ተደርጎባቸው እንዲጸድቁ የተከበሩ ተስፋዬ በልጂጌ (ዶ/ር) ጠይቀዋል፡፡ ምክር ቤቱም የብድር ስምምነቶቶቹ ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግረው እንዲጸድቁ የደገፈ በመሆኑ ዝርዝር ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ

በኢትዮጵያና በአፍርካ ልማት ባንክ መካከል ለአርብቶ አደሩ የምግብና የኑሮ ዘይቤ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1423/2018 በማድረግ በሙሉ ድምፅ አፅድቋል።

በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተደረገው የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1424 /2018 አድርጎ በአንድ ድምጸ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ ምክር ቤቱ አጽድቆታል፡፡

ምክር ቤቱ በውሎው የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን ለዝርዝር እይታ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴው መርቷል፡፡

የረቂቅ አዋጆችን አስፈላጊነት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ተስፋዬ ቤልጅጌ (ዶ/ር) ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

•የፌዴራል ታክስ አስተዳደር ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅን፣ የኢትዮጵያ የካርበን ገበያ ረቂቅ አዋጅን እና የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ረቂቅ አዋጅን ለፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ረቂቅ አዋጅን ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና የምግብ ስርዓትና ስርዓተ ምግብ ረቂቅ አዋጅን ለጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ቋሚ ኮሚቴ መርምረው ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ለዝርዝር እይታ መርቷል፡፡

## ክትትል ቁጥጥር

ምክር ቤቱ በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ግንቦት 04 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 20ኛ መደበኛ ጉባኤው የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት መቅደስ ዳባ (ዶ/ር) ከምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE



የጤና ተቋማት ተደራሽነት፣ የመድሃኒትና የህክምና ግብዓት አቅርቦት እና ስርጭትን ተደራሽነት በተመለከተ፤ የጤና ተቋማት በተያዘላቸው ጊዜ አለመጠናቀቅ ህብረተሰቡ አገልግሎት ለማግኘት እየተቸገረ እንደሆነ፣ የHIV በሽታ ስርጭት እና የቲቢ በሽታን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አኳያ እንዲሁም የእብድ ውሻ በሽታ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ የምክር ቤቱ አባላት አንስተዋል፡፡

የምክር ቤቱ አባላት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለፉት ወራት ያከናወናቸው ሥራዎች በሽታዎችን ከመከላከል ከመቆጣጠር እና ከማከም አንፃር አበረታች ውጤት መመዝገቡን ገልጸው፣ በበሽታ መከላከል፣ ክትባት ተደራሽነት፣ ወረርሽኝ ቅድመ መከላከልና የምርምር ተግባራት አበረታች ውጤት ማምጣቱን፣ የማርበርግ ቫይረስን በመከላከል እና መቆጣጠር የታየው ብቃት በሌሎች ተላላፊ በሽታዎችም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ምክር ቤቱ አመላክቷል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዘነጋ ያለ እና አምራች ዜጎችን የሚቀጥፍ የHIV እና የቲቢ በሽታን የመከላከል እና መቆጣጠር ብቃት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ተጠቁሟል።

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ በበኩላቸው የHIV እና የቲቢ በሽታዎችን የመከላከል እና የመቆጣጠር ሥራዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለረጅም ጊዜ ሲደገፍ ቢቆይም አገልግሎቱ በተቋረጠ ጊዜ ኢትዮጵያ ጠንካራ የጤና ሥርዓት በመገንባቷ ባለፉት ዓመታት በሽታዎችን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ አበረታታች ውጤት የተመዘገበ መሆኑን አብራርተዋል።

ሌላው በጤና ተቋማት ያሉ የግብዓት ችግሮችን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ከክልል ጤና ቢሮዎች፣ ከግል ጤና ተቋማት ጋር ልዩ ትኩረት በመስጠት የሚሰራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ዜጎች መሠረታዊ የጤና አገልግሎት በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ አዳዲስ የጤና ተቋማት ግንባታዎችን ከማካሄድ ጎን ለጎን፣ ነባር የጤና ተቋማት ያላቸውን አቅም የማሳደግና ደረጃቸውን የማሻሻል ሥራ በስፋት እየተሠራ መሆኑን፣ የጤና መድህን ሥርዓት በርካታ ዜጎችን ያቀፈና የአገልግሎቱ ፈላጊዎች ቁጥር ዕድገት የታየበት ሲሆን የግብዓት ዕጥረት እንዳይፈጥር በትኩረት እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

ከሚያስፈልገው የመድኃኒት አቅርቦት 70 በመቶ የሚሆነውን በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በኩል ለማሟላት እየተሠራ ሲሆን ቀሪው በመንግሥትና በግል አጋርነት የሚሸፈን ይሆናል ብለዋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

በ"ኢትዮጵያ ታምርት" ንቅናቄና ለሀገር ውስጥ አምራቾች በተሰጠው ድጋፍ፣ የሀገር ውስጥ የመድኃኒት አቅርቦት ድርሻም 46 በመቶ መድረሱ አመላክተዋል።

እንዲሁም ጠንካራ የጤና ፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋትና አሠራሮችን በማዘመን ለዜጎች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝም ሚኒስትሯ ጠቁመዋል።

በመጨርሻም ክብርት ዶክተር መቅደስ ዳባ በዘርፉ የሚሰጠውን አገልግሎት የበለጠ ለማሳደግና ተደራሽ እንዲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቀጣይ ትኩረት የሚያደርግባቸው አቅጣጫዎች ጠቁመው የመጀመሪያ ደረጃ ጤና እንክብካቤ ማጠናከር፣የባለሙያዎችን ብቃት ማጎልበት፣ የመረጃ ሥርዓቱን ማዘመንና ማጠናከር፣ የጤና ፋይናንስ ሥርዓቱን ማጠናከር እንዲሁም በሀገር ምርትና በሀገር ባለሙያ መጠቀም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራባቸው መሆኑን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ግንቦት 11 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 22ኛ መደበኛ ጉባኤው የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርን የ2018 በጀት ዓመት የ9 ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዳምጧል፡፡





የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ክቡር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) አቅርበዋል፡፡

ክቡር ሚኒስትሩ በቋሚ ኮሚቴውና በምክር ቤቱ አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡





የሰው ሀብት ስራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ነገሪ ሌንጮ(ዶ/ር) በቴክኖሎጂ የታነጸ የሰው ሀብት ለማፍራት ስልጠናዎች መሰጠታቸው፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮች መካሄዳቸው፣ በስፔስ ሳይንስና በጂኦ ስፓሻል ዘርፎች የተሰሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

አክለውም የንግድና የመንግሥት አገልገሎቶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ የተደረገበት፣ የፈጠራ ስራዎች የአዕምሮ ንብረት ባለቤትነት መብት ሰርተፊኬት መሰጠት መቻሉንና በቴክኖሎጂ ታግዞ የሀገሪቱን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የተደረገው ጥረት ተግባራት በጥንካሬ የሚታዩ አፈጻጸሞች ናቸው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የተከበሩ ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር) የሀገሪቱን ልማቶች ለማፋጠን የሚያግዝ ሳተላይት ለማምጠቅ እና የመንግስት አገልግሎቶችን

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝበ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

ይበልጥ ለማሳለጥ የጥሪ ማዕከል ለመገንባት በእቅድ ተይዘው በዘኝ ወራት ውስጥ ያልተፈጸሙ ተግባራት መሆናቸውን ጠቁመው መንግስት የጀመረውን የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ለማሳደግ፣ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 የተሳካ እንዲሆን፣ በስፔስ ሳይንስና በጂኦ ስፓሻል ዘርፍ ችግር ፈቺ ጥናቶች እንዲካሄዱ እንዲሁም የፈጠራ ሥራዎች ለኢትዮጵያ ብልጽግና የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዲችሉ ተቋሙ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል፡፡


ለበለጠ መረጃና አስተያየት

አድራሻ (Address)

ስልክ Tel:- 0111-13-49-70
ነፃ ስልክ ጥሪ Free call 8557
ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box : 80001
ኢ..ሜይል E-mail info@hopr.gov.et


በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የኮሙኒኬሽን፣ አስተህምሮና ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈፃሚ የተዘጋጀ፤